ቀን 25/04/16ዓ.ም

# ማስታወቂያ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፣ አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ እና ኖርዌጂያን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በጋራ ባላቸው የ Ethiopian Norwegian Network in Computational Mathematics (ENNCoMat) ፕሮጀክት በ2017 ዓ/ም በመደበኛዉ መርሀ ግብር ከዚህ በታች በተጠቀሱት ፕሮግራሞች በሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተማር ይፈልጋል።

1. Master of Science in Mathematical Modelling
   ፕሮግራሙ የሚሰጥበት ቦታ ፡-Arba Minch University
   ብዛት ፡- 1
2. Master of Science Degree in Applied Mathematics
   ፕሮግራሙ የሚሰጥበት ቦታ ፡_ Adama Science and Technology University
   ብዛት ፡- 1
3. Master of Science in Computational Mathematics
   ፕሮግራሙ የሚሰጥበት ቦታ ፡_ Hawassa University
   ብዛት ፡- 1

## <u>የማመልከቻ መስፈርቶች</u>

- አመልካቾች ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በተመሳሳይ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ድግሪ ያለዉ/ያላት
- በ 2016 ዓ.ም የGAT ፈተና ወስዶ/ዳ በትምህርት ሚኒስተር የተቀመጠውን የማለፊያ ነጥብ ያመጣ/ያመጣች
- አግባብነት ካላቸዉ ተቋማት 3 የድጋፍ ደብዳቤዎች ማቅረብ የሚችል/የምትችል
- ዩኒቨርሲቲዉ የሚያወጣዉን የመግቢያ ፈተና ማለፍ የሚችል/የምትችል
- ቀደም ሲል ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ኦፊሺያል ትራስክሪፕት ማስላክ የሚችል/የምትችል
- አግባብነት ካላቸዉ ተቋማት የስራ ልምድ ማቅረብ የሚችል/የምትችል
- የስፖንሰር ሽፕ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል የምትችል
- ኖርዌይ በሚገኘው ተባባሪ የኒቨርስቲ ከስድስት ወር እስከ አስር ወር ድረስ የሚሰጠውን የትምህርት ስልጠና ለመውሰድ ፍቃደኛ የሆነ/የሆነች እንዲሁም ለጉዞ የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች እስከ መጋቢት 30/2016 ዓ.ም ድረስ ማቅረብ የሚችል/የምትችል

ማሳሰቢያ፡-

- **ምዝገባው የሚከናወነው በኦላይን ብቻ ሲሆን ምንም አይነት ማስረጃ በአካል ይዞ በመቅረብ ማስገባት አይቻልም።**
- አመልካቾች ከታህሳስ 25-ጥር 17 /2016 ዓ.ም የማመልከቻ ፎርሙን በሚከተለው ቅጽ (https://forms.gle/m64cYX6qTK7dez8SA) ላይ በመግባት መረጃዎችን መሙላት ይጠበቅባቸዋል።
- አመልካቾች በ ፒዲኤፍ (PDF) ፎርማት የተለወጠ የትምህርት ማስረጃዎትን፣ የትምህርት ወጪዎን /Sponsorship/ የሚሸፍንልዎት የመንግስት መስሪያ ቤት የተፈረመበትና ማህተም የተደረገበት ፎርም እና ሌሎች መረጃዎችን በማያያዝ ምዝገባዎትን ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል።
- የመግቢያ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾች ከተማሩበት ተቋም ኦፊሺያል ትራስክሪፕታቸዉ ወደ አመለከቱበት ዩንቨርሲቲዉ ሬጅስትራርና አሉምናይ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ማስላክ የሚጠበቅባቸው ሲሆን በምዝገባ ወቅት ኦፊሻል ትራንስክሪፕት ካልደረሰ መመዝገብ አይችሉም።
- የመግቢያ ፈተና የሚሰጥበት ቀን በቀጣይ የሚገለጽ ይሆናል።
- የመግቢያ መስፈርቱን አሟልተው ያለፉ ተማሪዎች ባለፉበት ዩኒቨርስቲ ማሟላት ያለባቸውን መረጃ አሟልተው አድሚሽን የሚሰጣቸው ሲሆን በመጨረሻም ትምህርታቸውን ሲጨርሱ አድሚሽን ከሰጣቸው ዩኒቨርስቲ የትምህርት ማስረጃቸው የሚሰጥ ይሆናል።
- የመግቢያ መስፈርቱን አሟልተው ያለፉ ተማሪዎች ኖርዌይ ሂደው በሚማሩበት ጊዜ የሚኖሩበትንና የትራንስፖርት ወጪዎችን በውሉ መሰረት ፕሮጀክቱ የሚሸፍን ይሆናል።
- የመግቢያ መስፈርቱን አሟልተው ያለፉ ተማሪዎች ሀገር ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት ስፖንሰር የሌላቸው ከሆነ አነስተኛ የኪስ ገንዘብ ፣ የወጪ መጋራት ክፍያ ፣ የትምህርት ወጪዎችን እና የምርምር ወጪዎችን ፕሮጀክቱ የሚሸፍን ይሆናል።

ENNCoMat ፕሮጀክት አስተባባሪ